# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 21-31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እና 1-10፤ 11-20 ፌብርዋሪ 2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ - 3 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 3 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 4 -

ካርታ 3 ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 5 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 8 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -


እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

በጃንዋሪ የመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዴት 3.8፣ 4.0፤ በሐሮማያ -0.4፣ 1.2፣ 2.0፣ 4.4፣ 4.6፣ 4.8፣3.4፤ በአለም ከተማ 4.6፤ በአምባማሪያም 4.4፣ 4.0፤ በአርሲ ሮቤ 2.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 4.0፤ በባቲ 4.0 4.6፤ በቦሬ 3.6 በቡኢ 2.5፣ 2.0 3.4፣ 4.6፤ በደብረብርሀን 0.2፣ 2.2፣ 3.6፣4.8፤ በዳንግላ 4.0፣ 4.0 4.5፣ 3.0 4.0፤ በቢሾፍቱ 1.0፣ 1.1፣ 3.2፣ 3.6፣ 3.0፣ 4.0፤ በእምድብር 3.5፣ 3.1፣ 3.5፤ በጅግጅጋ 1.0፣ 2.0 0.6፣ 2.4፣ 4.0 4.2፣ 4.2፣ 4.3፤ በጅማ 3.4፣ 4.0፤ በመሐል ሜዳ 4.5፣ 4.0፤ በሾላ ገቢያ 4.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 3.0፣ 2.8፣ 4.1፣ 4.2፣ 3.4፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.0 ፤ እንዲሁም በወገል ጤና 2.2፣ 2.8፣ 3.6፣ 3.6፣ ፤ በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡





ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሸፋን አንፃር ሲገመገም በቴፒ 23.2፣ በወላይታ ሶዶ 13.4፣ በሰኮሩ 9.8፣ በማጂ 8.1፣ በብላቴ 7.8፣ በካቺሴ 6.4፣ በቦሬ 6.3፣ በጭራ 6.3፣ በኢጀጂ 6.3፣ በፍቼ 5.9፣ በጊምበ 5.3 እንዲሁም በወራቤ 5.3 ሚሜ የሚደርስ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በተለይም በመጀመሪያወቹ ቀናቶች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጥቂት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች በስተቀር ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3)፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 3 ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር


## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ ሶስተኛ አሥራ አንድ ቀናት በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ነበረዉ። በአንጻሩም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ መጠነኛ ቅዝቃዜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ተስተዉሏል። በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ቀናት በደቡብ ምዕራብና በተወሰኑ የደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን፤ የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈነው የጃንዋሪ ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት አብዛኛው የሀገራችን ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ቢሆኑም፤ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ ኪስ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር የውሃ ሀብት በመጠኑም ቢሆን አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 5)፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ገፅታ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ምስራቅ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 32 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት እና የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በመጪዎቹ አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በተለይም በሳምንቱ የመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ በሰሜን በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላትና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና የሚኖረዉ ሲሆን በተጨማሪም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በባሮ አኮቦ፣ በላይኛው ምስራቃዊ አባይ፣ የታችኛው ምስራቃዊ አዋሽ፣ በጥቂት ላይኛው ተከዜ እንዲሁም የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ የሚኖረው እርጥበት የገጸ ምድርን የውኃ ሀብትን በመጠኑም ቢሆን ያሻሽላል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ ተከዜ፣ መካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ ገናሌ ዳዋ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ለይ ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et